# በዲስትሪክቱ ውስጥ የሜዲኬር፥ ሜዲኬድና የረጅም ጊዜ አገልግሎትና ድጋፍ መርሃ ግብሮችን ማነጻጸር

| | ሜዲኬድ Fee-for-Service (FFS) (ክፍያ ለአገልግሎት) | ሜዲኬድ EPD waiver (ማስቀሪያ) | PACE መርሃ ግብር | Dual Choice (HIDE SNP) |
|---|---|---|---|---|
| *ይህ መርሃ ግብር ምንድነው?* | ሜዲኬድ fee-for-service (FFS) ሽፋን ማለት ግለሰቦች የግል ሜዲኬድ ጤና ዋስትና ውስጥ አልተመዘገቡም ማለት ነው፥ አንዳንድ ጊዜም “straight Medicaid” (“ቀጥተኛው ሜዲኬድ”) ተብሎ ይጠራል። | የሜዲኬድ EPD Waiver የአረጋውያንና የአከል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች መርሃ ግብር ነው። ይህ መርሃ ግብር በቤታቸው ውስጥ ወይም በማህበረሰባቸው መካከል መኖር ለሚፈልጉ ግለሰቦች የፋይል አስተዳደርና አገልግሎቶች ያቀርባል። | PACE ማለት Program of All-Inclusive Care for the Elderly (ለአረጋውያን ሁሉን አቀፍ የእንክብካቤ መርሃ ግብር) ነው። የሜዲኬርና የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞችን ከሕክምና ቅንጅት ጋር ያጣምራል። በተጨማሪም PACE በቤታቸው ውስጥ ወይም በማህበረሰባቸው መካከል መኖር የሚፈልጉ ሰዎችን ያገለግላል። | HIDE SNP ማለት Highly Integrated Dual Eligible Special Needs Plan (በከፍተኛ ሁኔታ የተቀናጀ በሁለት በኩል ብቃት ያለው የልዩ ሁኔታዎች ዋስትና) ነው። ይህ ሁለቱንም የሜዲኬር ጥቅማጥቅሞችንና የተወሰኑ ወይም በሙሉ የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞችን የሚሸፍን ዓይነት የጤና ዋስትና ነው። |
| *ለዚህ መርሃ ግብር ብቁነት አለኝ?* | ሰዎች ከFederal Poverty Limit (FPL) (የፌዴራል ድህነት ገደብ) እስከ 200 በመቶ በሚደርስ ገቢ ለሜዲኬድ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ሰዎች የተወሰኑ ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው (ለምሳሌ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ኗሪ መሆን)። | ለሜዲኬድ ብቁነት ያላቸው ሰዎችና አንዳንድ ከፍ ያለ ከSocial Security Insurance (SSI) (የሶሻል ሴክዩሪቲ ዋስትና) መደብ እስከ 300 በመቶ ገቢ ያላቸው ሰዎች፥ ለEPD ማስቀሪያ ብቃት ሊኖራቸው ይችላል። የረጅም ጊዜ እንክብካቤ መስጫ ተቋም (NF LOC) የእንክብካቤ መስፈርት ደረጃን ጨምሮ የተወሰኑ ሌሎች መመዘኛዎችን ማሟላት አለባቸው። የእንክብካቤ ደረጃውን እንደሚያሟሉ ለማወቅ ሰዎች መገምገም አለባቸው። ግለሰቦች በአንድ ጊዜ በEPD ማስቀሪያም በDual Choice (ዱዋል ቾይስ) ውስጥም መመዝገብ ይችላሉ። | የተወሰኑ ሌሎች መመዘኛዎችን እስካሟሉ ድረስ፥ ሰዎች በከፍተኛ ገቢ እስከ 300 በመቶው የSocial Security Insurance (SSI) መስፈርት ለPACE መርሃ ግብር ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሌሎች መመዘኛዎች ዕድሜ 55 ዓመት ወይም ከዛ በላይ መሆንና የረጅም ጊዜ እንክብካቤ መስጫ ተቋም (NF LOC) የእንክብካቤ መስፈርት ደረጃን ማሟላት ያካትታሉ። የPACE ተሳታፊዎች በPACE እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆንና መቻል እንዲሁም በማህበረሰብ ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መኖር መቻል አለባቸው። በPACE ውስጥ መመዝገብ የሚፈልጉ ሰዎች በPACE የአገልግሎት ክልል ውስጥ መኖር አለባቸው (ዎርዶች 7 እና 8)። | ለሁለቱም ለሜዲኬድና ለሜዲኬር ብቁ የሆኑ ሰዎች ለ Dual Choice መርሃ ግብር ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በ”ከፊል ጥቅም” ብቃት ያላቸው የ Qualified Medicare Beneficiaries (QMB) (ብቃት ያላቸው የሜዲኬር ተጠቃሚዎች) እንኳን Dual Choice ውስጥ ለመመዝገብ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ሰዎች የረጅም ጊዜ እንክብካቤ መስጫ ተቋም (NF LOC) የእንክብካቤ መስፈርት ደረጃን ማሟላት የለባቸውም፥ ሆኖም ማድረግ ይችላሉ። |
| *መርሃ ግብር ውስጥ እንዴት ነው የምመዘገበው?* | በሜዲኬድ ውስጥ ለመመዝገብ የዲስትሪክቱ ኗሪዎች የ DC Department of Human Services (DHS) Service Center (የዲሲ ሰብዓዊ አገልግሎቶች አገልግሎት ማዕከል) ጋር መሄድ ይችላሉ (https://dhs.dc.gov/service/find-service-center-near-you)። የDC Department of Aging and Community Living (DACL)ም (የዲሲ እርጅናና የማህበረሰብ ኑሮ መምሪያ) ዕድሜያቸው 60ና ከዛ በላይ ለሆኑ የዲስትሪክቱ ኗሪዎችና የአካል/አእምሮ ጉዳት ላላቸው ሰዎች የምዝገባ እገዛ ያቀርባል። | የDC Department of Aging and Community Living (DACL) (የዲሲ እርጅናና የማህበረሰብ ኑሮ መምሪያ) በEPD ማስቀሪያ ውስጥ መመዝገብ ለሚፈልጉ የዲስትሪክት ኗሪዎች የምዝገባ እርዳታ ያቀርባል። DACL ጋር በ202-724-5622 መደወል ይቻላል። DACL ማመልከቻ ለመሙላት ሰዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ያግዛል። አንድ ነርስ ወይም ማህበራዊ ሠራተኛ የአገልግሎቶች ፍላጎቶችን ደረጃ ለመወሰን ግምገማ ወይም ቃለ መጠይቅ ያካሂዳል። ይህ ግምገማ የEPD ማስቀሪያ ማመልከቻ ለማስገባት አስፈላጊ ነው። | የPACE መርሃ ግብር በ2022 ዓ.ም. ከተከፈተ በኋላ ሰዎችን ማስመዝገብ ይጀምራል። ሰዎች ግምገማና ወደ PACE ድርጅት ሪፈራል በማግኘት በPACE ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ። | በአሁኑ ጊዜ የሜዲኬር ሽፋናቸውን በተመለከተ የDual Choice ዋስትናን (ባሁኑ ጊዜ በ2021 ዓ.ም. United Health Care እና Cigna) የመምረጥ አማራጭ አላቸው። በ2022 ዓ.ም. ይህ ምርጫ የአንድ ሰው የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞች በቀጥታ ከሜዲኬር ጋርም ይካተታል ማለት ነው። ሰዎች የሜዲኬር ዋትና ደላላ የሆነው የState Health Insurance Program (202-727-8370)ን (የስቴት ጤና ዋስትና መርሃ ግብር) በመገናኘት የ Dual Choice ዋስትና ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ፥ ወይም እራሳቸው ዋስትናዎቹ ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ። |

*ልብ ይበሉ፡- ይህ ሰነድ ሁለቱንም ሜዲኬድንም ሜዲኬርንም ያነሳል። ሜዲኬድ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ወይም ሌሎች መመዘኛዎች ለሚያሟሉ ሰዎች የሕክምና ዋስትና የሚያቀርብ በስቴቶች የሚተዳደር መርሃ ግብር ነው – በዚህ ጉዳይ ላይ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግሥት። ሜዲኬር በዩ ኤስ ፌዴራል መንግሥት የሚንቀሳቀስ መርሃ ግብር ሲሆን ዕድሜያቸው 65 ወይም ከዛ በላይ ለሆኑ ወይም ሌሎች መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ማንኛውም ገቢ ላላቸው ብቃት ላላቸው ሰዎች ሽፋን ያቀርባል። ሰዎች ለሁለቱም መርሃ ግብሮች ብቁ ሆነው በእያንዳንዱ ሥር የተለያዩ አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ።*

| | ሜዲኬድ Fee-for-Service (FFS) (ክፍያ ለአገልግሎት) | ሜዲኬድ EPD waiver (ማስቀሪያ) | PACE መርሃ ግብር | Dual Choice (HIDE SNP) |
|---|---|---|---|---|
| *በመርሃ ግብሩ ውስጥ ምን ምን ተሸፍኗል?* | የሜዲኬድ መርሃ ግብር ሁሉንም ሕክምና፥ የዶክተር፥ የሆስፒታልና ዶክተር ያዘዛቸው መድኃኒቶችን ጨምሮ ይሸፍናል። መርሃ ግብሩ ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን እንደ ጥርስ ሕክምና፥ የጆሮ ማዳመጫና የረጅም ጊዜ ሕክምናን ይሸፍናል። አንድ ሰው ሁለቱም ሜዲኬርም ሜዲኬድም ካለው እነዚህ ሁለቱ መርሃ ግብሮች የሕክምናውን ወጪ ይጋራሉ። | የEPD ማስቀሪያ ውስጥ የተመዘገቡ ሰዎች ሁሉንም ሕክምና፥ የዶክተር፥ የሆስፒታልና ዶክተር ያዘዛቸው መድኃኒቶችን የሚያካትት የሜዲኬድ ሽፋን አላቸው። ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን እንደ ጥርስ ሕክምና፥ የጆሮ ማዳመጫና የረጅም ጊዜ ሕክምናንም ይሸፍናል። አንድ ሰው ሁለቱም ሜዲኬርም ሜዲኬድም ካለው እነዚህ ሁለቱ መርሃ ግብሮች የሕክምናውን ወጪ ይጋራሉ። የEPD ማስቀሪያ ለሌሎች የሜዴኬድ ተመዝጋቢዎች የማይቀርቡ ጥቅማጥቅሞች ያቀርባል። እነዚህም የፋይል አስተዳደርን፥ የአዛውንቶች ኑሮ ድጋፍና በተሳታፊ ላይ ያተኮሩ አገልግሎቶችን ያካትታሉ። | የPACE መርሃ ግብር ሁሉንም ሜዲኬርና ሜዲኬድ የሚሸፍናቸውን አገልግሎቶች ይሸፍናል። ይህም ዶክተሮችን፥ የሆስፒታል ሕክምናንና ዶክተር ያዘዘውን መድኃኒት ያካትታል። ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን እንደ ጥርስ ሕክምና፥ የጆሮ ማዳመጫና የረጅም ጊዜ ሕክምናን ይሸፍናል። ብዙዎቹ በPACE የሚቀርቡ አገልግሎቶች በPACE ማዕከል ውስጥ ባንድ ቦታ ላይ ነው የሚሰጡት። የPACE ማዕከል የቀን መርሃ ግብሮችና ሌሎች በቦታው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለምሳሌ የምግብ አገልግሎት ያቀርባል። የPACE መርሃ ግብር ለሌሎች የሜዲኬድ ተመዝጋቢዎች የማይቀርቡ ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ሊያቀርብ ይችላል። ሆኖም የPACE መርሃ ግብር በEPD ማስቀሪያ ሥር የሚቀርቡትን አገልግሎቶች በሙሉ ላያቀርብ ይችላል። | የDual Choice መርሃ ግብር ሁሉንም በሜዲኬር የተሸፈኑ አገልግሎቶች ዶክተሮች፥ የሆስፒታል ሕክምና፥ ዶክተር ያዘዘውን መድኃኒት ጨምሮ ይሸፍናል። በ2022 ዓ.ም. የሜዲኬድ ጥቅማጥቅሞችንም ስለሚያካትት ሌሎች አገልግሎቶችን እንደ ጥርስ ሕክምና፥ የጆሮ ማዳመጫና የረጅም ጊዜ ሕክምናንም ያካትታል። እንደ ግለሰቡ የሜዲኬድ ብቁነት ጥቅማጥቅሞች ሊለያዩ ይችላሉ። እያንዳንዱ Dual Choice የጤና ዋስትና ለሌሎች የሜዲኬርና የሜዲኬድ ተመዝጋቢዎች የማይቀርቡ ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ሊያቀርብ ይችላል። |
| *የፋይል አስተዳዳሪ ወይም የሕክምና አስተባባሪ ይኖረኛል?* | አንዳንድ በሜዲኬድ ውስጥ የተመዘገቡ ሰዎች የሕክምና አስተባባሪ ሊኖራቸው – ማለትም በሕክምና አሰሳ ላይ እገዛ። My Health GPS እና My DC Health Home ዓይነት መርሃ ግብሮች ይህን ዓይነት እርዳታ ያቀርባሉ። ሌሎች በሜዲኬድ ውስጥ የተመዘገቡ ሰዎች ለምሳሌ አረጋውያንን የሚያገለግሉ ዓይነት በማህበረሰብ ላይ ከተመሠረቱ ድርጅቶች እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ። ከዚህ ውጪ ብዙ የሜዲኬድ ተመዝጋቢዎች የፋይል አስተዳዳሪም ሆነ የሕክምና አስተባባሪ የላቸውም። | የEPD ማስቀሪያ የፋይል ማስተዳደርን እንደ አገልግሎት ያካትታል። የፋይል ማስተዳደር የEPD ማስቀሪያ ግዴታ የሆነ አካል ነው፡- ተመዝጋቢዎች በፋይል አስተዳደር ውስጥ መሳተፍ አለባቸው። የአንድ ሰው ፋይል አስተዳዳሪ የብዙ የተለያዩ ነገሮች ኃላፊነት አለበት። እነዚህም የዕቅድ ማውጫ አገልግሎቶችን፥ የሜዲኬድ ምዝገባን ለመጠበቅ እርዳታ መስጠትን፥ ሕክምና አቅራቢዎች ጋር ማስተባበርና ሌሎችንም ያካትታል። | የPACE መርሃ ግብር በሕክምና ማስተባበር አቀራረቡ ለየት ያለ ነው። በPACE ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው በሕክምናው የሚያግዘው የ11 ሰው ቡድን ይኖረዋል። ቡድኑ እንደ ዶክተር፥ ማህበራዊ ሠራተኛ፥ ቴራፒስትና ሌሎችም ዓይነት ከተለያዩ መስኮች የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያካትታል። የዚህ ዓይነት አቀራረብ ዓላማ አገልግሎቶችን በቦታው ለማቆየት፥ ከተመዝጋቢው ግለሰብ ጋር ለመነጋገርና የግለሰቡን ፍላጎቶች ለማሟላት ነው። | Dual Choice የፋይል አስተዳደርን እንደ አገልግሎት ያካትታል። የፋይል አስተዳደር ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው የሚያስፈልጋቸውን ሕክምና ፈልገው እንዲያገኙ በሚረዱ በተለዩ ባለሙያዎች ቡድን ይቀርባል። የእንክብካቤ ቡድኑ ሕክምናን የማቀድ፥ የሜዲኬድ ምዝገባን መጠበቅ፥ ከሕክምና አቅራቢዎች ጋር ማቀነባበርና ሌሎችም ነገሮችን የመርዳት ኃላፊነት አለበት። የEPD ማስቀሪያ ውስጥ ሁለት ቦታ ለተመዘገቡ ዓይነት ለአንዳንድ ሰዎች የፋይል አስተዳደር ግዴታ ነው። |
| *አሁን ያለኝ ዶክተር ጋር መቆየት እችላለሁ?* | ብዙ ዲስትሪክት ውስጥ ያሉ ዶክተሮች በሜዲኬድ ውስጥ ይሳተፋሉ፥ የሜዲኬድ ታካሚዎችንም ይቀበላሉ። ሁሉም ዶክተሮች ይህን አያደርጉም ስለዚህ ዶክተርዎ ይህን ያለማድረግ ዕድል አለው። ካሳሰብዎት ዶክተርዎ በሜዲኬድ ውስጥ እንደሚሳተፍ መጠየቅ ይችላሉ ወይም የሜዲኬድ አገልግሎት ሰጪ ማውጫ ውስጥ በ www.dc-medicaid.com ማየት ይችላሉ። እንዲሁም የDC Department of Health Care Finance (DHCF) ጋር በ 202-698-2000 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ። | የEPD ማስቀሪያ የሜዲኬድ ሽፋን ያቀርባል። ይህ ማለት ሜዲኬድ ያላቸው በEPD ማስቀሪያ ውስጥ የሚመዘገቡ ሰዎች ሽፋናቸውን (እና ዶክተሮቻቸውን) ያስቀራሉ። ለሜዲኬድ አዲስ ለሆኑ ሰዎች፥ ዶክተርዎ(ሮችዎ) ላይሳተፍ ይችላል። ካሳሰብዎት ዶክተርዎ በሜዲኬድ ውስጥ እንደሚሳተፍ መጠየቅ ይችላሉ ወይም የሜዲኬድ አገልግሎት ሰጪ ማውጫ ውስጥ በ www.dc-medicaid.com ማየት ይችላሉ። የDC Department of Health Care Finance (DHCF) ጋር በ 202-698-2000 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ። | የPACE መርሃ ግብርን ልዩ የሚያደርገው "ሁሉንም የሚያካትት" በመሆኑና መርሃ ግብሩ የራሱ ሕክምና አቅራቢዎች ዶክተሮችን ጨምሮ አሉት። በዲስትሪክቱ ውስጥ አንዳንድ ዶክተሮችና አገልግሎት አቅራቢዎች ከ PACE መርሃ ግብር ጋር ውል ሊፈራረሙና በPACE ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማገልገል ሊቀጥሉ ይችላሉ። ሁሉም ዶክተሮች ይህን አያደርጉም ስለዚህ የእርስዎ ዶክተር ይህን ላያደርግ ይችላል። ካሳሰብዎት PACE ውስጥ ከመመዝገብዎ በፊት ዶክተርዎ የ PACE ተሳታፊዎችን ያክም እንደሆነ ይጠይቁት። የማያክም ከሆነ አዲስ ዶክተር መምረጥ ይኖርብዎታል። | የDual Choice መርሃ ግብር የሚንቀሳቀሰው በጤና ዋስትናዎች ነው። እንደ ማንኛውም የጤና ዋስትና እነዚህ ድርጅቶች የራሳቸው የአገልግሎት አቅራቢና የዶክተር አውታረመረቦች አላቸው። ብዙ በዲሲ ውስጥ የሚሠሩ ዶክተሮች የDual Choice መርሃ ግብር አባል ሊሆኑ ይችላሉ። ካሳሰብዎት ዶክተርዎ የDual Choice ወይም የMedicare Advantage ተሳታፊዎችን ያክም እንደሆነ ይጠይቁት። የማያክም ከሆነ አዲስ ዶክተር መምረጥ ይኖርብዎታል። |

ልብ ይበሉ፡- ይህ ሰነድ ሁለቱንም ሜዲኬድንም ሜዲኬርንም ያነሳል። ሜዲኬድ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ወይም ሌሎች መመዘኛዎች ለሚያሟሉ ሰዎች የሕክምና ዋስትና የሚያቀርብ በስቴቶች የሚተዳደር መርሃ ግብር ነው – በዚህ ጉዳይ ላይ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግሥት። ሜዲኬር በዩ ኤስ ፌዴራል መንግሥት የሚንቀሳቀስ መርሃ ግብር ሲሆን ዕድሜያቸው 65 ወይም ከዛ በላይ ለሆኑ ወይም ሌሎች መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ማንኛውም ገቢ ላላቸው ብቃት ላላቸው ሰዎች ሽፋን ያቀርባል። ሰዎች ለሁለቱም መርሃ ግብሮች ብቁ ሆነው በእያንዳንዱ ሥር የተለያዩ አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ።

| | **ሜዲኬድ** Fee-for-Service (FFS) (**ክፍያ ለአገልግሎት**) | **ሜዲኬድ** EPD waiver (**ማስቀሪያ**) | PACE **መርሃ ግብር** | Dual Choice (HIDE SNP) |
|---|---|---|---|---|
| *የተወሰነ ሰፈር ውስጥ መኖር አለብኝ?* | በሜዲኬድ ውስጥ ተመዝግበው ሽፋንዎን ለማቆየት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ኗሪ ለመሆንዎ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። ሆኖም በዲስትሪክቱ ውስጥ በማንኛውም ቦታ መኖር ይችላሉ። | በEPD ማስቀሪያ ውስጥ ተመዝግበው ሽፋንዎን ለማቆየት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ኗሪ ለመሆንዎ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። ሆኖም በዲስትሪክቱ ውስጥ በማንኛውም ቦታ መኖር ይችላሉ። | የPACE መርሃ ግብር በዎርዶች (ወረዳዎች) 7 እና 8 ለሚኖሩ ሰዎች ብቻ ነው። በእነዚህ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ኗሪዎች ብቻ ናቸው መርሃ ግብሩ ውስጥ መመዝገብ የሚችሉት። በወረዳዎች 7 ወይም 8 ውስጥ የሚኖሩ ከሆነና በPACE ከተመዘገቡ በኋላ ወደ ሌላ ወረዳ ለቅቀው ቢሄዱ የPACE ብቁነትዎ ያበቃል። ወደፊት ዲስትሪክቱ የአገልግሎት ክልሉን ወደተጨማሪ ወረዳዎች ያስፋፋ ይሆናል። | በDual Choice ማስቀሪያ ውስጥ ተመዝግበው ሽፋንዎን ለማቆየት የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ኗሪ ለመሆንዎ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎት። ሆኖም በዲስትሪክቱ ውስጥ በማንኛውም ቦታ መኖር ይችላሉ። |
| *ለማንኛውም ነገር መክፈል አለብኝ?* | ሜዲኬድ ካልዎት ክፍያ (ወይም "ኮፔይ") የሚያስፈልገው ብቸኛው አገልግሎት በሀኪም የታዘዘ መድኃኒት ነው። መድኃኒት ቤቱ ኮፔይ ከጠየቅዎትና የመክፈል አቅሙ ከሌልዎት አልችልም ማለት ይችላሉ፥ ይህም ሆኖ መድኃኒትዎ ይሰጥዎታል። | የEPD ማስቀሪያ ምዝገባ የሜዲኬድ ሽፋንን ያካትታል። ክፍያ (ወይም "ኮፔይ") የሚያስፈልገው ብቸኛው አገልግሎት በሀኪም የታዘዘ መድኃኒት ነው። መድኃኒት ቤቱ ኮፔይ ከጠየቅዎትና የመክፈል አቅሙ ከሌልዎት አልችልም ማለት ይችላሉ፥ ይህም ሆኖ መድኃኒትዎ ይሰጥዎታል። | PACE ተሳታፊዎችን ምንም ዓይነት የጋራ ክፍያ ወይም ኮፔይ ማስከፈል አይችልም። | ሜዲኬድ ካልዎት ክፍያ መጋራት ወይም ኮፔይ አያስፈልግም። ይበልጥ ውስን ሽፋን ያላቸው ሰዎች (ለምሳሌ ሙሉ የሜዲኬድ ሽፋን የሌላቸው Qualified Medicare Beneficiaries (ብቃት ያላቸው የሜዲኬር ተጠቃሚዎች) ወይም QMBዎች ለአንዳንድ አገልግሎቶች መክፈል ይኖርባቸው ይሆናል። |
| *በመርሃ ግብር ውስጥ ሌሎች ኃላፊነቶች አሉብኝ?* | ሜዲኬድ ብዙ ጥቅማጥቅሞች አሉት፥ ሰዎችም በመርሃ ግብሩ ውስጥ በርካታ መብቶች አሏቸው። እንዲሁም የተወሰኑ አስፈላጊ ኃላፊነቶች አሏቸው። በመጀመሪያ የግል መረጃዎን – የመገናኛ መረጃ፥ የገቢና የንብረት መረጃ – በመርሃ ግብሩ ውስጥ ወቅታዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪ የሜዲኬድን ደንቦች ማወቅ (ምን እንደሚፈቀድና ምን እንደማይፈቀድ) እና ስለ ጤናዎና ስለ ሕክምና አቅራቢዎችዎ ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሕክምና ቡድንዎ ተሳታፊ አባል መሆን ይችላሉ፥ መሆን አለብዎትም፥ እንዲሁም ችግሮች ወይም አሳሳቢ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ መነጋገር ያስፈልጋል። | የEPD ማስቀሪያ የሜዲኬድ ሽፋንን ያካትታል፥ ብዙ መብቶችና ኃላፊነቶችም ተመሳሳይ ናቸው። አዲስ የማስቀሪያ ተመዝጋቢዎች በምዝገባው ወቅት የመብቶችና የኃላፊነቶች ዝርዝር ይሰጣቸዋል። የማስቀሪያ ተመዝጋቢዎች የፋይል አስተዳዳሪ ሊኖራቸው ይገባል እንዲሁም ምንም ዓይነት ሌላ የማስቀሪያ አገልግሎቶች ባይጠቀሙም፥ ከፋይል አስተዳዳሪያቸው ጋር መነጋገር አለባቸው። በEPD ማስቀሪያ ውስጥ ያሉ ሰዎች ማንኛውም ጥያቄ፥ አቤቱታ ወይም ሐሳብ ሲኖራቸው የፋይል አስተዳዳሪያቸውን እንደ "መጀመሪያ መድረሻ" መጠቀም አለባቸው። | PACE የሜዲኬድና የሜዲኬር ሽፋን ያካትታል። አዲስ የPACE ተመዝጋቢዎች በምዝገባው ወቅት የመብቶችና የኃላፊነቶች ዝርዝር ይሰጣቸዋል። ልክ እንደ EPD ማስቀሪያ፥ የPACE ተሳታፊዎች የእንክብካቤ ቡድን ይመደብላቸውና ምንም እንኳን ብዙ የሕክምና አገልግሎቶች ባይጠቀሙም የሕክምና ቡድናቸውን ማነጋገር አለባቸው። የPACE ተመዝጋቢዎች ማንኛውም ጥያቄ፥ አቤቱታ ወይም ሐሳብ ሲኖራቸው የሕክምና ቡድናቸውን እንደ "መጀመሪያ መድረሻ" መጠቀም አለባቸው። | የDual Choice ተመዝጋቢዎች በምዝገባው ወቅት የመብቶችና የኃላፊነቶች ዝርዝር ይሰጣቸዋል። ከሌሎቹ መርሃ ግብሮች ጋር በተመሳሳይ መልኩ፥ የሕክምና ቡድን ይመደብልዎታል፥ ምንም እንኳን ብዙ የሕክምና አገልግሎቶች ባይጠቀሙም የሕክምና ቡድንዎትን ማነጋገር ይኖርብዎታል። አንዳንድ Dual Choice ውስጥ ያሉ ሰዎች የሕክምና ቡድን እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ ይኖርባቸዋል (ለምሳሌ የEPD ማስቀሪያ ተመዝጋቢዎች)። ተሳታፊዎች ማንኛውም ጥያቄ፥ አቤቱታ ወይም ሐሳብ ሲኖራቸው የሕክምና ቡድናቸውን እንደ "መጀመሪያ መድረሻ" መጠቀም አለባቸው። |
| *ካስፈለገኝ አሁንም ወደ ድንገተኛ ክፍል መሄድ እችላለሁ?* | ሜዲኬድ ሁሉንም የድንገተኛ ክፍል ሕክምና ያለምንም ወጪ መጋራት ወይም ኮፔይ ይሸፍናል። የሜዲኬርም የሜዲኬድም ሽፋን ካልዎት የሕክምናዎን ወጪ እነሱ ይካፈሉታል። | የEPD ማስቀሪያ የሜዲኬድ ሽፋንን ያካትታል። ሜዲኬድ ሁሉንም የድንገተኛ ክፍል ሕክምና ያለምንም ወጪ መጋራት ወይም ኮፔይ ይሸፍናል። የሜዲኬርም የሜዲኬድም ሽፋን ካልዎት የሕክምናዎን ወጪ እነሱ ይካፈሉታል። | PACE ሁሉንም በሜዲኬርና በሜዲኬድ የተሸፈኑ አገልግሎቶችን፥ የድንገተኛ ክፍል ሕክምናን ጨምሮ ይሸፍናል። ይህ መርሃ ግብር ድንገተኛ ሕክምና በሚያስፈልግዎት ጊዜ ይረዳዎታል፥ ሆኖም ሆስፒታል ሳይሄዱ ሊረዳዎት ይችል እንደሆነ ለማየት PACE ከሥራ ሰዓት ውጪ ሌሎች አገልግሎቶችን ሊሰጥዎ ይችላል። | Dual Choice የድንገተኛ ክፍል ሕክምናን ያለምንም ወጪ መጋራት ወይም ኮፔይ ይሸፍናል። ሜዲኬርና ሜዲኬድ የሕክምናዎን ወጪ ይካፈሉትና እርስዎ ማድረግ እንዳይኖርብዎት ሕክምናዎንና ጥቅማጥቅሞችዎን ያቀነባብርልዎታል። |

ልብ ይበሉ፡- ይህ ሰነድ ሁለቱንም ሜዲኬድንም ሜዲኬርንም ያነሳል። ሜዲኬድ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ወይም ሌሎች መመዘኛዎች ለሚያሟሉ ሰዎች የሕክምና ዋስትና የሚያቀርብ በስቴቶች የሚተዳደር መርሃ ግብር ነው – በዚህ ጉዳይ ላይ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግሥት። ሜዲኬር በዩ ኤስ ፌዴራል መንግሥት የሚንቀሳቀስ መርሃ ግብር ሲሆን ዕድሜያቸው 65 ወይም ከዛ በላይ ለሆኑ ወይም ሌሎች መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ማንኛውም ገቢ ላላቸው ብቃት ላላቸው ሰዎች ሽፋን ያቀርባል። ሰዎች ለሁለቱም መርሃ ግብሮች ብቁ ሆነው በእያንዳንዱ ሥር የተለያዩ አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ።

| | **ሜዲኬድ** Fee-for-Service (FFS) (**ክፍያ ለአገልግሎት**) | **ሜዲኬድ** EPD waiver (**ማስቀሪያ**) | PACE **መርሃ ግብር** | Dual Choice (HIDE SNP) |
|---|---|---|---|---|
| *መርሃ ግብሩ ለእኔ ትክክል እንዳይልሆነ ከወሰንኩ መተው እችላለሁ?* | የሜዲኬድ ተመዝጋቢዎች በማንኛውም ጊዜ መልቀቅ ይችላሉ። ምዝገባውን መተው ከመረጡ የሜዲኬድ ሽፋኑ ያበቃል። ሰዎች ከምዝገባው መውጣት መፈለጋቸውን ለDC Department of Human Services (DHS) ማስታወቅ ይችላሉ። ሁለቱም ሜዲኬድም ሜዲኬርም ካልዎት ከሜዲኬድ ምዝገባ መውጣት የሜዲኬር ሽፋንዎ ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም። | የEPD ማስቀሪያ ተመዝጋቢዎች በማንኛውም ጊዜ መልቀቅ ይችላሉ። ሆኖም ሜዲኬድን ማግኛ መንገድዎ ከማስቀሪያ ሽፋን ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ከማስቀሪያው መውጣት ከፈለጉ የሜዲኬድ ሽፋንዎ ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ለማወቅ የፋይል አስተዳዳሪዎን ያነጋግሩ። ሁለቱም ሜዲኬድም ሜዲኬርም ወይም ሌላ የጤና ዋስትና ካልዎት ከሜዲኬድ ምዝገባ መውጣት የሜዲኬር ሽፋንዎ ወይም የሌላ ሽፋንዎ ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም። | የPACE ተመዝጋቢዎች በማንኛውም ጊዜ መልቀቅ ይችላሉ። ሆኖም ሜዲኬድን ማግኛ መንገድዎ ከPACE ምዝገባዎ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። PACEን መልቀቅ ከፈለጉ፥ የሜዲኬድ ሽፋንዎን ወይም የሌላ ሽፋንዎን ማቆየት ይችሉ እንደሆነ ለማወቅ ከመርሃ ግብሩ ጋር መነጋገር ይኖርብዎታ። ሁለቱም ሜዲኬድም ሜዲኬርም ወይም ሌላ የጤና ዋስትና ካልዎት ከሜዲኬድ ምዝገባ መውጣት የሜዲኬር ሽፋንዎ ወይም የሌላ ሽፋንዎ ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም። | የDual Choice ተመዝጋቢዎች የመልቀቅ መብት አላቸው፥ ሽፋናቸውንም በሶስት ወር አንድ ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ሆኖም ከ2022 ዓ.ም. ጀምሮ ስለ Dual Choice የሚያደርጓቸው ውሳኔዎች ሁለቱንም ሜዲኬርም ሜዲኬድም ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል። Dual Choiceን ለሜዲኬድ ብለው ትተው ለሜዲኬር ብለው ማቅየት አይችሉም። ለውጦች ካደረጉ ሁለቱም የሽፋን አማራጮች መቀየር ይኖርባቸዋል። |

ልብ ይበሉ፦ ይህ ሰነድ ሁለቱንም ሜዲኬድንም ሜዲኬርንም ያነሳል። ሜዲኬድ ገቢያቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ወይም ሌሎች መመዘኛዎች ለሚያሟሉ ሰዎች የሕክምና ዋስትና የሚያቀርብ በስቴቶች የሚተዳደር መርሃ ግብር ነው – በዚህ ጉዳይ ላይ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ መንግሥት። ሜዲኬር በዩ ኤስ ፌዴራል መንግሥት የሚንቀሳቀስ መርሃ ግብር ሲሆን ዕድሜያቸው 65 ወይም ከዛ በላይ ለሆኑ ወይም ሌሎች መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ማንኛውም ገቢ ላላቸው ብቃት ላላቸው ሰዎች ሽፋን ያቀርባል። ሰዎች ለሁለቱም መርሃ ግብሮች ብቁ ሆነው በእያንዳንዱ ሥር የተለያዩ አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ።